➢ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ

➢ ለዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብት መከበር የሚደረገውን ትግል ለምትደግፉ የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ አባላት

እኛ ከግንቦት 1997 ብሔራዊ ምርጫ ጋር ተያይዞ በተፈጠረ ችግር ምክንያት "እነ አቶ ኃይሉ ሻውል" በሚል የክስ መዝገብ በጥቅል የከተሰስነው የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የአመራር አባላት፣ አባላትና ጋዜጠኞች የቀረበብን የፈጠራ ክስ ምንም ህጋዊ መሠረት የሌለው የፖለቲን ክስ በመሆኑ በክሱ ሂደት ውስጥ ገብተን ለአለመከራከር ወስነናል፡፡ ይህንኑ ውሳኔያችንን ለማብራራት ያዘጋጀነውን ሰነድ ታህሳስ 26 ቀን 1998 ዓ.ም. ጉዳዩን ለሚመለከተው የከፍተኛው ፍ/ቤት ሁለተኛ ችሎት በንባብ ለማሰማት ብንሞክርም ፍ/ቤቱ እንዳናሰማ ከልክሎናል፡፡ ስለሆነም ለኢትዮጵያ ህዝብ፣ ለዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብት መከበር የሚደረገውን ትግል ለሚደግፈው የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ አባላት ውሳኔያችን እንዲደርስ የሰነዱን ሙሉ ይዘት አቅርበናል፡፡

ቀን 26-4-98

<< ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለተኛ ወንጀል ችሎት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ በፍርድ ቤቱ የክስ ሂደት የማንሳተፍ መሆናችንን ስለመግለጽ፡፡

እኛ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ አመራሮችና አባላት፣ እንዲሁም የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች የሆን "እነ ኃይሉ ሻውል" በሚል የክስ መዝገብ ሰባት የተለያዩ ክሶች ተመስርተውብን በእስር ላይ መሆናችን ይታወቃል፡፡

የቀረበብንን ክስ፣ ከታሰርን ጊዜ ጀምሮ ያለውን የፍርድ ሂደት እና በሀገራችን ያለውን የዳኝነት ስርዓት በመገምገም እንዲሁም ዘላቂ ሠላምና ዲሞክራሲ በሀገራችን የሚሰፍንበትን መንገድ በመመልከት የሚከተለውን ሀተታ እና መቃወሚያ እናቀርባለን፡፡

## 1. ክሶቹ ከፖለቲንዊ ምክንያት የመነጩ ስለመሆናቸው፤

ዐቃቤ-ህግ አሁን በእኛ ላይ ለቀረበው ክስ መነሻ የሆነው ግንቦት 7/1997 ዓ.ም. በተደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ የህዝብ ድምፅ መሠረቅን ተከትሎ በሀገራችን የተፈጠረው ፖለቲካዊ ክስተት ነው፡፡ ለጉዳዩ እልባት ለመሥጠት ተቃዋሚ ፓርቲዎችና መንግስት በተደጋጋሚ ውይይት ቢያደርጉም ገዢው ፓርቲ የዲሞክራሲ መርሆችን ለማክበር ፈቃደኛ ባለመሆኑ እና የሰብዓዊ መብትና የፖለቲካ ጥያቄዎችን በኃይል ለመጨፍለቅና ከዚህ አቋሙ ፈቀቅ ለማለት ባለመፈለጉ የተነሳ የተፈጠረ ችግር ነው፡፡

የቀረበውም ክስ መንግስት የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን እና ነፃ ጋዜጠኞችን ከፖለቲካ መድረክ ለማስወገድ የቀረበ እንጂ በፍርድ ሂደት መልስ የሚያገኝና የሚያስከስስ የወንጀል ድርጊት ስለተፈፀመ የቀረበ አይደለም፡፡ ይህም ለመሆኑ የሚከተሉት ነጥቦች ያረጋግጣሉ፡፡

1.1. ከጥቅምት 22/98 ዓ.ም በፊት በመንግስትና በቅንጅት መካከል ተደጋጋሚ ውይይቶች ተደርገዋል:: ቅንጅትም የምርጫውን ሂደትና የተከሰቱ ችግሮችን እንዲሁም የህዝብን ድምጽ ለማስከበር የሚከተላቸውን የትግል ስልቶች አስመልክቶ በርካታ መግለጫዎችን አውጥቷል:: የግል ጋዜጦችም ሆኑ የመንግስት መገናኛ ብዙኃን ይህንኑ አሰራጭተዋል::

ቅንጅት የተጠቀመባችወ የትግል ስልቶች በዓለም በሙሉ የታወቁና የሚሠራባቸው የሥልጡን ህዝብ መለኪያዎች የሆኑ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አካሎች ናቸው::

በመጨረሻ ጊዜ መንግሥት እንዲያሟላቸው በቅንጅት የቀረቡ 8 ጥቄዎችም በህገ-መንግሥቱ የተደነገጉ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ዕውን መሆን አስተማማኝ መሠረቶች መሆናቸው በዓለም አቀፍ ሚዛን ዕውቅና ያገኙ ዐበይት ጉዳዮች እንጂ ዐቃቤ ህጉ በክሱ ላይ እነደገለፀው ህገ-መንግስታዊውን ሥርዓት በኃይል ለመናድ ተግባር የሚውሉ አይደሉም::

ቅንጅት ለዲሞክራሲ መስፈንና ስልትም አልባ ለሆነው ሥልጣን ማክተም በሚያደርገው ትግል ስለገፋበትና ከኢህአዴግ መሪዎች ለሚደርስበት ማስፈራራት ሰለአልተንበረከከ ለህግ አልባው ሥርዓት ህልውና አስጊ ተብሎ ተፈርጆ የፈጠራ ወንጀል ክስ በእኛ ላይ ተመስርቶብናል::

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ገና ከመከሰሳችን በፊት በተለያዩ ጊዜያት በሰጧቸው ይፋ መግለጫዎች ፓርላማ የማንገባ ከሆነ ያሉን አማራጮች ከአገር መሰድድ፣ ጠብ-መንጃ አንስቶ መታገል፣ አንገት ደፍቶ መቀመጥ፣ ወይም ዕድሜ ልክ በዕስር መማቀቅ ብቻ እንደሆነ አረጋግጠውልናል:: ሰለዚህ ፓርላማ የማንገባ ከሆነ ዕድሜ ልክ እስራት የሚያሳስር የህግ አንቀጽ ተጠቅሶ የምንከሰስ፣ በሎም የዋስ መብት ተነፍገን በእስር የምንማቅቅ መሆኑን አስቀድሞ በጠቀላይ ሚኒስትሩ የተሰጠ ብይን ነው::

በሌላ አነጋገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራሳቸው ከሳሽ፣ ራሳቸው ምስክር፣ ራሳቸው ዳኛ ሆነው ተከሳሾች ወንጀለኞች ናቸው ብለው በይፋ አስቀድመው ፍርድ ሰጥተዋል:: ሰለዚህ ዓቃቤ ህግ በጠቅላይ ሚንስትሩ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ያቀረበው ክስ ከፖለቲካዊ ምክንያት የመነጨ ለመሆኑ ክሱ ከመቅረቡ በፊት የተረጋገጠ ነበር:: ይህም በመሆኑ ነው ዐቃቤ ህጉ ለሙያው ታማኝ ከመሆን ይልቅ በታሪክና በትውልድ ፊት የሚያስጠይቀውን መንገድ መርጦ ቅንጣት ታክል የክስ አቀራረብ ህግን ይልተከተለ የሀሰት ክስ የመሠረተብን::

በእኛ በኩል ሀገራችንን ጥለን የማንሰደድ፣ ጠብ-መንጃ ይዘን የማንታገል፣ ነገር ግን በምንም ዓይነት በሀገራችን ያለ ነጻነት አንገታችንን ደፍተን የማንኖር መሆናችንን ሲያረጋግጡ አይን ባወጣ አምባገነናዊነት ወደሌላው አማራጫቸው፣ ማለትም ወደ እስር ቤት ወርውረውናል::

1.2. ቅንጅት አንደ ፓርቲ ባሳለፋቸው ድርጅታዊ ውሳኔዎች ይህ ክስ ሲቀርብ የውሳኔው አካል የሆንን አመራር ለሁለት ከፍሎና አንደኛውን ወገን ለይቶ መክሰስ ቅንጅትን ከፋፍሎ ለማጥቃትና ለማዳከም የታቀደ በፖለቲካዊ ልዩነት ላይ የተመሠረተና ምንም የህግ መሠረት የሌለው የፈጠራ ክስ መሆኑን ያሳያል::

1.3. ከተከሳሾች ውስጥ ከፊሎቻችን በጥቅምት መጨረሻ ላይ ከተፈጠረው ክስተት በኋላ ፓርላማ እንድንገባና ሌሎችም እንዲገቡ እንድናስተባብር ተጠይቀን ፈቃደኛ ባለመሆናችን እና ፓርቲያችን ላቀረባቸው የፍትህ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች መፈጸም በትግላችን በመግፋታችን ተከሰናል:: ከሌሎቹ ጋር አብረን ከመከሰስ ወይም የተጠየቅነውን ከመፈፀም እንድንመርጥ ተገደን በያዝነው ፖለቲካዊ አቋም በመጽናታችን ምክንያት መከሰሳችን ለክሱ ፍጹም ፖለቲካዊነት ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው::

1.4 ከተከሳሾች መካከል ከፊሎቻችን ደግሞ በትግል አጋሮቻችን ላይ እንድንመሰክር ተጠይቀን በሀሰት ለመመስከር ፈቃደኛ ባለመሆናችን የተከሰስን ነን:: ይህም በከሳሾቻችን በኩል በርካታ የሀሰት ምስክሮችን የመመልመልና የማሠልጠን ሥራ በሠፊው እየተሠራ መሆኑን ያመለክታል::

1.5. ከተከሳሾች ውስጥ ከምሥራቅ ጎጃም ተይዘን የቀረብነው ተከሳሾች የድርጅቱ አባላት ከመስከረም 15/1998 ዓ.ም. ጀምሮ በእስር ላይ መሆናችን እየታወቀ ጥቅምት 22 እና 23/98 ዓ.ም. የተፈጠረውን ፖለቲካዊ ክስተት ቀስቅሳችኋል ተብለን የተከሰስነው ከቅንጅት አደራጅነታችን እንድናፈገፍግ በቀረበልን መደለያ ተታለን፣ በተሠነዘረብንም ማስፈራሪያ ተሸንፈን ከትግሉ ስላልወጣን ብቻ ነው::

1.6 የግል የመገናኛ ብዙኃን አባሎች በጅምላ የተከሰስነው በልዩ ልዩ የፕሬስ ውጤቶች መነሻነት ነው:: በመሰረቱ የፕሬስ ውጤቶች በሙሉ ሀሳብን በነጻነት የመግለጫ መድረኮች ሲሆኑ በውስጣቸውም አንዳችም የወንጀል ይዘት የላቸውም::

በፕሬስ ውጤቶች አማካኝነት ወንጀል ተፈፅሟል ቢባል እንኳን ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የፕሬስ ድንጋጌዎች መሠረት ክስ ይቀርብ እንደሆን ነው እንጂ አሁን የፌዴራል ዐቃቤ ሀግ ያቀረባቸው ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል የመናድ እና የሀገር ክህደት ወንጀል ክሶች አንዳችም የህግ መሠረት የላቸውም:: አንድ የፕሬስ ውጤትን በመጠቀም ኃላፊነትን የሚያስከትል ጥፋት ተፈፅሟል ቢባል እንኳን ክስ የሚቀርበው ኃላፊ ነው በተባለው ሰው ላይ ብቻ ይሆናል:: ይህ አሠራር የሌሎች በኃላፊነት መጠየቅ ያስቀራል:: አሁን በመንግስት እየተወሰደ ያለው እርምጃ ግን በዋና አዘጋጅ፣ በምክትል ዋና አዘጋጅ፣ በሪፖርተሮች፣ በባለንብረትና በአሳታሚ ድርጅቶች ላይ ሁሉ በጅምላ መወንጀል ነው::

ይህም የክሱ መነሻና መድረሻ ሀሳብ ነፃ የህዝብ አስተያየት የሚንሸራሸርበትን የግል ፕሬስ እንደተቋም ጭምር ለማጥቃት እና ለማጥፋት ያለመ ፖለቲካዊ እርምጃ መሆኑን ያረጋግጣል::

## 2. በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የያዘ ክስ ያልቀረበ ስለመሆኑ፤

2.1. በግንቦት 97 ምርጫ የህዝብ ድምፅ መሠረቅን ተከትሎ የተፈጠረ ክስተት ላይ ተመስርቶ የተቀነባበረው የፈጠራ ክስ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን እና የግል ጋዜጠኞችን በእስር ለማማቀቅ፣ ለማዳከምና ብሎም ለማጥፋት የተዘጋጀ ሥልት ነው:: የወንጀል ክስ አቀራረብ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111፣ 112 እና 113 ላይ በግልፅ ተደንግጓል:: አሁን የቀረበው ክስ ግን ከእነዚህ ድንጋጌዎች እንዱንም ያላሟላና ገዢውን ፓርቲ ለማስደሰት የቀረበ ነው::

የወንጀል ጥፋቶች ናቸው ተብለው የቀረቡት ጉዳዮች በወንጀል ህግ በተመለከተው መሠረት አንድ የወንጀል ተግባርን የማያቋቁሙ ናቸው:: የህግ ፍሬ ነገሮችን (Legal Ingredients) እና ግዙፋዊ ነገሮችን (Material Ingredients) በአንድነት አሟልተው አይገኙም:: በምክንያትና በውጤት መካከል የታወቁ ግንኙነቶች መኖራቸውን አያስረዱም:: ወንጀል ተፈፀመ የሚባልበትን ቦታና ጊዜ በማያሻማ ሁኔታ ለይተው አይገልጹም:: በጥቅሉ ክሶቹ ከወንጀል ህግ መሪ ድንጋጌዎች ውጪ አጠቃላይ በሆኑ አነጋገሮች ብቻ ተከሳሾችን በጅምላ የሚወነጅሉ ናቸው:: ክሶቹ የእያንዳንዱን ተከሳሽ የወንጀል ተሳትፎ (Criminal Participation) ያላስቀመጡ፣ ተፈፀሙ የተባሉት ወንጀሎ በማን፣ በምን፣ መቼ፣ የት፣ እንዴት፣ እንደተፈፀሙ በግልፅ ያላስረዱ፣ ገዢዎች ለማሰር የፈለጉትን ሰው ማሰርና ማሠቃየት እንዲችሉ ሲባል ክስ እንዲዘጋጅ ሰላዘዙ ብቻ የተዘጋጁ ናቸው::

2.2. ለማስረጃነት የቀረቡ ሰነዶች ማለትም የፓርቲ መመሥረቻ ፅሁፎች፣ የፓርቲ መተዳደሪያ ደንቦች፣ የምርጫ ማኒፌስቶ፣ በምረጡኝ ዘመቻ ወቅት የቀረቡ የፖለቲካ ክርክሮች እና የመሳሰሉት ሲሆኑ አቀራረባቸውም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓተ ህግ የሚደነግገውን የሚፃረር ነው::

የፖሊስና ደህንነት አባላት ለብርበራ ወደ ተከሳሾች ቢሮዎችና መኖሪያ ቤቶች ሲሄዱ ተከሳሾችን ለመወንጀል የሚያስችሉ የሀሰት ማስረጃዎችን ይዘው በመግባት በብርበራው ወቅት እንደተገኙ በማስመሰል አቅርበዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ከምሥራቅ ጎጃም የመጡ ተከሳሾችን በደብረ-ማርቆስ ከተማ ደህንነትና ፖሊስ አባላት ከፖሊስ መጋዘን ካወጡት ጠብ-መንጃና ጥይት ጋር አስገድደው በቪዲዮ እንዲቀረፁ አድርገዋቸዋል። በአጠቃላይ የተለያዩ የሀሰት ሰነዶች ተዘጋጅተው በማስረጃነት ቀርበዋል።

ጽ/ቤቶቻችን ልክ በጦርነት እንደተያዘ የጠላት ይዞታ ከህግ ውጪ ተሰብረው በደህንነት አባለትና በመከላከያ ሠራዊት በቁጥጥር ሥር ውለው ነበር። በጽ/ቤቶቻችን ውስጥ ይገኙ የነበሩ ሰነዶችና ሌሎች ንብረቶች እንደምርኮ ንብረት ተግዘዋል። እነዚህ መረጃዎች አሁን እነዴትና በምን ሁኔታ በማስረጃነት እንደሚቀረቡብን አናወቅም:: ለምሣሌ ከጽ/ቤቶቻች በተወሰዱ በርካታ ኮምፒውተሮች ውስጥ ያሉ ሠነዶች እኛን ለመወንጀል ይጠቅመናል ባሉት መንገድ ለውጠው ማቅረብ ይችላሉ።

## 3. የዳኝነት ሥርዓቱ ለገዢው ፓርቲ የግል መጠቀያ ስለመሆኑ፤

ተከሳሾች እጃች ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በጊዜ ቀጠሮ፣ በዋስትና ጥያቄ እና አሁንም ደግሞ በዋናው የክስ መዝገብ ለበርካታ ጊዜያት ፍ/ቤት ቀርበናል። ነገር ግን ተከሳሾች በወንጀል ክርክር ውሥጥ ከከሳሹ ጋር በዳኝነት እኩል የመታየት መብት አላቸው የሚለው አለም አቀፍ የህግ መርህ በዚህ ፍ/ቤት ተጥሶ እኛ ተከሳሾች ተጠቂ ሆነን እንድንቀርብ መድረኩ ለከሳሻችን ተመቻችቶለታ። ፍ/ቤቱ ከዓጋቤ ህጉ በላይ እኛን ከመሞገትና መብታችንን ከመርገጥ በቀር የእኛን ጥያቄ ለማዳመጥ ዝገጁ ሆኖ አልተገኘም።

አልፎ አልፎም በተራ ጉዳች ላይ የሠጣቸውን ትዕዛዞች እንኳን ፖሊስ አልፈፅምም ሲል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት ለምን እንዳልፈፀመ መርምሮ ትዕዛዙን ማስከበር ሲገባው የፖሊስን እና የዐቃቤ ህግን አቋም እያየ የሰጣቸውን ትዕዛዞች ያነሳል፡፡ አልያም  በዝምታ ያልፋል፡፡ ይህ ፍ/ቤት የተጠቂዎች ከለላና መከታ መሆን ሲገባው በተቃራኒው የባለ ጠብመንጃዎች ተጨማሪ የጥቃት መሳሪያ ሆኖላቸዋል፡፡

ይህ ፍ/ቤት የመንግስትን ሥልጣን ያለአንዳች ልጓም የያዘው ኢህአዴግ የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን እና በራሱ አምሳል አልቀረፅ ያሉትን ነፃ ጋዜጦችን ለማጥፋት የተያያዘው ተግባሩ እንዲሳካት የማስመሰያ የህግ ሽፋን በመስጠትና ከህግ ውጪ የተከሳሾች የዋስ መብት በምንፈግ አመቺ ሆኔታ ፈጥሮለታል፡፡

በመሠረቱ ክሱ የፈጠራ ቢሆንም አስተማማኝ ዳኝነት የምናገኝ ቢሆን ኖሮ ገዢውን ፓርቲ የምናጋልጥበት ሌላ የትግል መድረክ ይሆንልን ነበር፡፡ ሆኖም ግን የከዚህ ቀደሙ ተሞክሯችንም ሆነ ዛሬ እየተፈፀመ የምናየው ድርጊት የሚያሳየን ካለው የህግ ሥርዓት ፍትህ ያማናገኝ መሆናችንን ነው፡፡

የምርጫ ቦርድና ፍ/ቤቶች ከገዢው ፓርቲ ተፅዕኖ ነፃ ያለመሆናቸውን ብንገነዘብም ለህግና ለሥርዓት ባለን አክብሮት በምርጫው ሂደት የተከሰቱ የማጭበርበር ተግባራት በፍ/ቤት እንዲጣሩ ቅንጅት በቅንነት ጥረት አድርጓል፡፡  ለአብነት ያህል የምርጫ ቦርዱ ሕግን በመፃረር ጊዜያዊ የምርጫ ውጤት እያለ በየምሽቱ በመገናኛ ብዙኃን የሚሰጠው መግለጫ እንዲቀር ለፍ/ቤት አመልክቶ ፍ/ቤቱ ግን የቦርዱን ህገ-ወጥነት በማፅናት ወስኗል፡፡

በሌላም በኩል ግንቦት 7/1997 ዓ.ም. የምርጫው ዕለት ምሽት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህገ-መንግስቱን በመጻረር ከሥልጣቸው ውጪ ጊዜያዊ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ አብዛኛዎቹን የፖለቲካ መብቶች በማገዳቸው ቅንጅት ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታ አቀረበ፡፡ ፍ/ቤቱ አቤት ባይ ቅንጅትንና መልስ ሰጪ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ሳይጠራና ግራና ቀኙን ሳያከራክር ፋይሉን ዘጋው፡፡

እነዚህ የፍ/ቤቱ ውሳኔዎች በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ነፃ የመንግስት ዘርፍ አለመሆናቸውና ውሳኔዎቻቸው በማስረጃና በህግ ላይ የተመረኮዙ ሳይሆን በመንግስት ትዕዛዝ ላይ ብቻ የተመሠረቱ በመሆናቸው አይነተኛ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

በመሆኑም ተከሳሾች የፍትህ ሥርዓቱ ለገዢዎች የማስመሰያ መሣሪያ እንዲሆን ተባባሪዎች አንሆንም፤ ፖሊስን፣ ዐቃቤ ህግን እና ፍ/ቤቶችን የግል መጠቀሚያው አድርጎ በያዘ የግፍ ሥርዓት በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርቦ መከራከር ከገዢዎች ጋር አብሮ በፍትህ መቀለድ ይሆናል፡፡  ስለሆነም አሁን የተያዘው የፍ/ቤት ክርክር ትርጉም የሌለውና የገዢውን ፓርቲ ፍላጎት ለማሳካት የተዘጋጀ መድረክ በመሆኑ በክሱ ሂደት የማንሳተፍ መሆናችንን እንገልጻለን፡፡ >>

በሀገር ውስጥና በውጪ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን፣ በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የምትሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት እንዲሁም የኢትዮጵያን ህዝብ የዴሞክራሲ፣ የፍትህና የመልካም አስተዳደር ጥማት ተረድታችሁ እያደረግነው ባለው ትግል ከጎናችን ለቆማችሁ የዓለም-አቀፍ ማህበረሰብ አባላት፣ ታዋቂ ግለሰቦችና የፖለቲካ መሪዎች እንዲሁም ለሰብዓዊ መብቶችና ለጋዜጦች ደህንነት የቆማችሁ ድርጅቶች በሙሉ ለዓላማችን መሳካት ላደረጋችሁልን አስተዋፅኦ ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን። የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄዎች መልስ እስኪያገኙ ድረስም ከጎናችን እንደምትቆሙ እንተማማናለን።

ኢህአዴግም በጉልበት፣ በጭፍን ጥላቻ፣ በእልህ ህዝብን በመፍጀትና በማሸበር ለመግዛት የሚያደርገውን እኩይ ተግባር ለራሱ ጭምር እንደማይበጀው ተገንዝቦ ወድ ሠላማዊ የድርድር መድረክ እንዲመለስ ጥሪ እናደርጋለን። ሠላም ወዳድ የሆናችሁና የትግል አጋሮቻችሁ የተሰዉለትን ዓላማ ለጊዜያዊ ሥልጣን ለመገበር የማትፈልጉ የኢህአዴግ አባላት አሁን የሚደረገው የዴሞክራሲ ትግል አካል ናችሁ ብለን ስለምናምን ድርጅታችሁን ዛሬ እናንተ ነገ ደግሞ ልጆቻችሁ የሚኖሩባትን ሀገር ወደ ከፍተኛ ቀውስ ለማስገባት መሪዎቻችሁ በሚያደርጉት የጥፋት ጉዞ ተባባሪ አለመሆናችሁን ለማሳየት ድፍረቱ ይኑራችሁ እንላለን።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!! ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲና ለመልካም አስተዳደር መስፈን እንዲሁም ለሰበዓዊ መብቶች መከበር የምናደርገውን ሠላማዊ ትግል አሁን በዕስር ላይ ያለነውም ሆንን ከዕስር ውጪ የምንገኝ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች አጠንክረን እንቀጥልበታለን። ስለሆነም ገዢው ፓርቲ ለውይይትና ለድርድር እስከሚቀርብ ድረስ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገራት የተጀመረው ሠላማዊና ህጋዊ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን።